## አጀንዳ ቁጥር 7

## ሲ.ቭክ ማህበራትና መገናኛ ብዙሃን በአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንባታ ሂደት ያላቸውን ሚና መገምገም፤

### 1. ሲ.ቭክ ማህበራት

በዚህ አጀንዳ ዙሪያ በተደረገው ውይይት በቅድሚያ ሲ.ቭክ ማህበራት ከተቋቋሙበት ዓላማና ከሚወክሉት ጥቅም አንፃር በይዘታቸው የተለያዩ ስለሆኑ በውይይት መድረኩ ላይ ግምገማው ያተኮረባቸው ከፖለቲካ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሲ.ቭክ ማህበራት ብቻ ነው፡፡ በአንድ አገር ላይ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ሊጠናከር የሚችለው የህብረተሰቡን የተለያዩ ጥቅሞችና ፍላጐቶች የሚወክሉ ሲ.ቭክ ማህበራት በሚፈለገው መጠንና ይዘት ሲኖሩ ቢሆንም በአገራችን የሚገኙት ማህበራት በቁጥርም ሆነ በይዘት ከሌሎች አገሮች ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር በጣም ጥቂትና ደካማ በመሆናቸው እንዳሉ የሚቆጠሩ እንዳልሆነ ግምገማው በቅድሚያ ተማምኖበታል፡፡ ለዚህም የሕዝቡ የሶሺዮ-ኢኮኖሚ ደረጃ ዝቅተኛ መሆን ማለትም አብዛኛው የአገራችን ሕዝብ አርሶ አደርና በተለያዩ ጥቅሞች ሊወከል የማይችል መካከለኛ ገቢ ያለው /middle class/ ህብረተሰብ አለመሆኑ በዋና ምክኒያትነት የተጠቀሰ ሲሆን በወቅቱ የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩ ሲ.ቭክ ማህበራት በአግባቡ እንዳይጠናከሩ በማድረግ ረገድም የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዝ ተጠቅሷል፡፡

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የአንድ ሕዝብ ጥንካሬ የሚለካውና ጥቅሙም በተገቢው መንገድ ሊወከልና ሊጠበቅ የሚችለው በሲ.ቭክ ማህበራት ዙሪያ ተደራጅቶ በፖለቲካ ኃይሎች ላይ በሚያሳድረው ጫናና ግፊት ቢሆንም ይህ ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መጠናከር የማይተካ ሚና ያለው ቁምነገር በአገራችን እንዳለ የሚቆጠርበት ደረጃ ላይ አይገኝም፡፡ በአገራችን ከሚገኙ አብዛኛዎቹ ሲ.ቭክ ማህበራት በምርጫ ወቅትና በህግ አወጣጥ ሂደት በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ተፅእኖ ለማሳደር የሚችሉ የሕዝብ ነፃ ተቋማት ሳይሆኑ - በተቃራኒው የፖለቲካ ኃይሎች ለራሳቸው ጥቅምና ፍላጐት የሚጠቀሙባቸው ነፃነት የለሽ ተቋማት ሆነው ይታያሉ፡፡ በአገራችን ከተቋቋሙበት ዓላማ አንፃር ኃላፊነታቸውን በነፃነት ለመወጣት የሚሞክሩ አንዳንድ ሲ.ቭክ ማህበራት መኖራቸው ባይካድም አብዛኛዎቹ ማህበራት ግን እንወክለዋለን ለሚሉት ህብረተሰብ ሳይሆን በደርግ ጊዜ ይታይ እንደነበረው ግልፅ የሆነ የፖለቲካ ወገንተኝነት ይዘው የሚንቀሳቀሱ ተቋማት እንደሆኑ በግሃድ ይታያል፡፡

ሲ.ቭክ ማህበራት ለአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ግንባታ የማይተካ ሚና ያላቸው መሆኑን አምኖ በመቀበል መንግሥት እነዚህ ተቋማት በነፃነትና በገለልተኝነት የሚሰሩበትን ምቹ ሁኔታ ከማመቻቸት ይልቅ የራሱ የፖለቲካ መሣሪያና መጠቀሚያ እንዲሆኑ በሚያስችል ዘዴ ሆን ብሎ ስለሚያደራጃቸው ሚናቸው የአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚያጠናክር ሳይሆን በተቃራኒው የሚያደናቅፍ ሆኖ ይታያል፡፡ እንዲያውም አሁን አሁን በአንዳንድ የገዥው ፓርቲ ሰነዶች ላይ እንደሚታየው እንደ አንድ የፓርቲ መዋቅር ማህበራትም በፓርቲ እቅድና በጀት ተይዞላቸው የሚደራጁ አካላት እየሆኑ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ምንም እንኳ በአገሪቱ ያሉ ተቃዋሚ

ፓርቲዎች እንደገኸው ፓርቲ ለራሳቸው ጥቅምና ፍላጐት የሚሰሩ ሲቭክ ማህበራትን የማቋቋም አቅም የሌላቸው ቢሆንም አንዳንዶቹ ሲቭል ማህበራት ከተመሠረቱበት ዓላማ አንፃር የሚዛመዱ እንቅስቃሴዎችን ብቻ እያካሄዱ ከሥርዓቱ የሚቃጣባቸውን ተፅእኖ በአግባቡ መቋቋም ሲገባቸው ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ያላነሰ የከረረ የፖለቲካ አቋም በመያዝ ሥርዓቱን ሲያወግዙ ስለሚስተዋሉ በሂደት የገለልተኝነት ሚናቸው በሕዝቡ ዘንድ ጥያቄ ውስጥ እየገባ ከመምጣቱ በተጨማሪ እራሳቸውን ለገዥው ፓርቲ ጥቃት አመቻችተው ሲያቀርቡ እንደሚታይ ግምገማው ጠቁሟል፡፡ ሲቭክ ማህበራቱ በአገራችን እንደሚገኙ ሌሎች ተቋማት ከፍተኛ የግልፅነትና የተጠያቂነት ተግባር ያለባቸው ሲሆኑ - አንዳንዶቹ ማህበራትም የግለሰቦች ዝናና ጥቅም ማጋበሻ ሆነው እንደሚያገለግሉ ግምገማው ጠቁሟል፡፡

በአገራችን ሲቭክ ማህበራት በሚፈለገው መጠንና ይዘት ተጠናክረው በመገኘት ለዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚገባቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት የሚችሉት በዋናነት ከሕዝቡ የሶሽዮ-ኢኮኖሚክ የእድገት ደረጃና ከአጠቃላዩ ሕዝብ የፖለቲካ ባህል መዳበር ጋር በተያያዘ ቢሆንም አሁን ባለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የሚጠበቅባቸውን ሚና በአግባቡ እንዲጫወቱ -

- ሕዝቡ የሲቭክ ማህበራት በዴምክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የሕዝቡን ጥቅም በማስጠበቅ ረገድ ያላቸው ሚና ምትክ የሌለው መሆኑን በመገንዘብ በተለያዩ ጥቅሜንና ፍላጐቴን ይወክላሉ በሚላቸው ማህበራት ዙሪያ ተደራጅቶ ሊያጠናክራቸው እንደሚገባ፤

- መንግሥት እነዚህን ማህበራት የራሱ የፖለቲካ ጥቅም ማስከበሪያ ተቋማት ለማድረግ ከመፈለግና ከመስራት ይልቅ በነፃነትና በገለልተኝነት ከተመሠረቱበት ዓላማ አንፃር እየሠሩ ለአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንዳለበት፣

- ማህበራቱም የተቋቋሙበትን ዓላማ በተለያዩ ምክኒያቶች ዘንግተው የፖለቲካ ኃይሎች መጠቀሚያ ከመሆን ይልቅ ከፖለቲካ ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ኃላፊነታቸውን በመወጣት የሕዝቡን የተሟላ እምነት ማግኘት እንዳለባቸውና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው ተገቢውን ሚና መጫወት እንደሚገባቸው ግምገማው ጠቁሟል፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሠረት ሕዝቡ፣ መንግሥትና እራሳቸው ማህበራቱ የየድርሻ ኃላፊነታቸውን በትክክል መወጣት የማይችሉ ከሆነ ግን በአገራችን የመድበለ ፓርቲም ሆነ አጠቃላዩ የዴምክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው ሂደት እጅግ አዝጋሚ ሆኖ ሊቀጥል እንደሚችል ግምገማው አመላክቷል፡፡

## 2. መገናኛ ብዙሃን

መገናኛ ብዙሃንን በተመለከተ በተደረገው ግምገማ መድረኩ የመንግሥትና የግል መገናኛ ብዙሃንን በተናጠል ለመገምገም ሞክሯል፡፡ እንደ ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ የመገናኛ ብዙሃንም በሚፈለገው መጠንና ይዘት በአገራችን ተጠናክሮ ሊገኝ የሚችለው ከአገሪቱ

አጠቃላይ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ  የእድገት ደረጃና ከፖለቲካ ባህል መዳበር ጋር ተያይዞ ቢሆንም - አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የመገናኛ ብዙሃን የሚጠበቀውን ያህል ጠንካራ እንዳልሆኑና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው ሂደትም ሊኖራቸው የሚገባቸውን ሚና በአግባቡ እየተወጡ እንዳልሆነ፤ እንዲያውም አንዳንዶቹ የመገናኛ ብዙሃን በተቃራኒው የዴሞክራሲን እድገት አደናቃፊ የሆነ አሉታዊ ሚና እየተጫወቱ መሆኑን ግምገማው ጠቁሟል።

የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በምርጫ ወቅት ለተቃዋሚ ፓርቲዎችም መድረክ ለመስጠት የሚያደርጉት ሙከራ፣ መንግሥት የሚያከናውናቸውን በጐ ነገሮች ለሕዝቡ በማሳወቅ ረገድ ያላቸው ከፍተኛ ሚናና በተለያዩ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች (በተለይም የብሔር-ብሔረሰቦችን ባህል በማስተዋወቅ ረገድ) የሚሰሯቸው ፕሮግራሞች በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በጐ ጉንነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ነጥቦች መሆናቸውን ግምገማው አምኖበታል።

ነገር ግን እነዚህ ተቋማት በሕዝብ ኃብት የተቋቋሙ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ቢሆኑም ከምርጫ ውጭ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሃሣብ አብዛኛውን ጊዜ የማያስተናግዱ መሆናቸው፣ በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ከገዥው ፓርቲ አቋም የተለዩ ነፃ የሕዝብ አስተያየቶችን በስፋት የማያቀርቡ መሆናቸው፣ በውስጣቸው የሚሰሩ ጋዜጠኞች ግልፅ የሆነ የፖለቲካ ወገንተኝነት አቋማቸውን የሚያንፀባርቁ መሆናቸው፣ የዜናና የተለያዩ ፕሮግራሞች አቀራረባቸው ከሌሎች አገሮች የጥራት ደረጃ ጋር የሚመጣጠን ብቻ ሳይሆን የሚቀራረብ አለመሆኑ፤ አብዛኛዎቹ ፕሮግራሞች በአገሪቱ ውጤታማ የሆኑ ጉዳዮችን (success stroy) ብቻ እንጂ ሌሎች በአገሪቱ የሚታዩ ድክመቶችንና ችግሮችን በሚዛናዊነት የማያቀርቡ መሆናቸው፣ በአጠቃላይም የሚያቀርቧቸው ፕሮግራሞቻቸው  በደረቅ ፕሮፓጋንዳ የተሞሉና ለገዥው ፓርቲ የሚያደሉ በመሆናቸው ምክኒያት የመደመጥ መስህብ የሌላቸውና የሕዝብን አመኔታ ያጡ መሆናቸው በመንግሥት የመገናኛ ብዙሃን ዙሪያ በደካማ ጉንነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ዋና ዋና ነጥቦች መሆናቸውን ግምገማው ጠቁሟል።

የመንግሥት  መገናኛ ብዙሃን በደርግ ጊዜ የነበረውን ስልት በመከተል ሙሉ በሙሉ የገዥው ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ ሆነው መቀጠላቸው በአንድ በኩል ሕዝቡ ስለአገሩ ጉዳይ እውነተኛ መረጃ ለማግኘት ሲል ትኩረቱን ወደ ውጭ አገር መገናኛ ብዙሃንና ወደግል ፕሬሱ እንዲያደርግ ግፊት የፈጠረ ሲሆን - በሌላ በኩል ደግሞ የግል ፕሬሶች በሕዝቡ ውስጥ የተፈጠረውን የመረጃ ክፍተት በማየት በአብዛኛው የመንግሥትን ደካማ ጉን በመተቸትና በማሳጣት ላይ ብቻ እንዲያተኩር የሚያስችል ምክኒያት እንደፈጠረላቸው ግምገማው አሰቀምጧል። በአጠቃላይም - የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን የገዥው ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ሆነው የሚያገለግሉ፣ በአሰራራቸው ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና ሚዛናዊነት የሌላቸው፤ በዚህ አይነቱ ግልፅ የሆነ የአድሏዊነት ተግባራቸውም የሕዝቡን እምነት ያጡና ሕዝብና መንግሥትን በማራራቅ ረገድም ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ መሆኑን ግምገማው ገልፆ - ወደፊትም በእነዚህ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ዙሪያ ያለው አጠቃላይ አሰራር መሠረታዊ ለውጥ እንዲኖረው እስካልተደረገ ድረስ ገዥው ፓርቲ የቱንም ያህል በጐ ነገር ቢሠራ በሕዝቡ ዘንድ ከልብ የመደመጥና የመታመን እድሉ እጅግ ጠባብ ሆኖ እንደሚቀጥል ያለውን ስጋት ገልጿል።

በተመሣሣይ ሁኔታ መድረኩ የግል መገናኛ ብዙሃንን ለመገምገም ባደረገው ሙከራ - በቅድሚያ በቅርቡ ሁለት የግል FM ሬዲዮ ጣቢያዎች ስራ ከመጀመራቸው በፊት ለአለፉት 17 ዓመታት ከግል ጋዜጦች በስተቀር የግል የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙሃን የሚባል በአገሪቱ ስላልነበር የግምገማው ትኩረት በዋናነት የግል ጋዜጦች ላይ እንዲሆን ስምምነት ላይ ደርሷል፡፡ የግል ጋዜጦች ከመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በተለየ የመንግሥትን ድክመትና ጉድለቶች በድፍረት በማጋለጥ፣ ለተቃዋሚ ፓርቲዎችና ለሌሎች ነፃ አስተሳሰብ ላላቸው የህብረሰብ ክፍሎችና ግለሰቦች መድረክ በመፍጠር፣ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች የተለያዩ ነፃ አስተሳሰቦች በማስተናገድና ህብረተሰቡን በማስተማር፣ በተወሰነ ደረጃም የህብረተሰቡን የንባባ ባህል በማዳበር ረገድ ለአለፉት 17 ዓመታት የተጫወቱት ሚና በግል ጋዜጦች ዙሪያ በጠንካራ ጎንነት የሚታይ እንደሆነ ግምገማው አምኖበታል፡፡

አሁንም ተመሳሳይ ሚና በመጫወት ላይ የሚገኙና ገለልተኛ አቋም ይዘው ሕዝቡን ለማገልገል የሚሞክሩ ጥቂት ጋዜጦች በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ቢሆንም "አብዛኛዎቹ" ለአለፉት 17 ዓመታት ለህትመት የበቁት የግል ጋዜጦች ግን ሚናቸው ዴምክራሲንና የሃሣብ ነፃነትን የሚፃረር እንደነበረ ግምገማው ጠቁሟል፡፡ አብዛኛዎቹ የግል ጋዜጠኞች "ጋዜጠኛ" ለመባል የሚያበቃ ሥነ-ምግባርና እውቀት ያልነበራቸው፣ ከመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በተቃራኒ መንግሥትን በጭፍን የሚተቹና ተቃዋሚውን ጐራ በጭፍን የሚደግፉ፣ ያለምንም ተጨባጭ መረጃ የአገርን፣ የድርጅትንና የግለሰብን ስም የሚያጐድፍ የፈጠራ ወሬ የሚያሰራጩ፣ ለአገር ብሔራዊ ደህንነት ደንታ የሌላቸውና ዋና አላማቸው በርካሽ ፕሮፓጋንዳ ገንዘብ መሰብሰብን ያደረጉ እንደሆኑ ግምገማው ጠቁሟል፡፡ እነዚህ ጋዜጦች ህብረተሰቡ በአሁኑ ወቅት የተካረረ የፖለቲካ አቋም እንዲይዝና የአገራችን ፖለቲካ ከብሔራዊ መግባባትና ከምክኒያታዊ ፖለቲካ እንዲርቅ በማድረግ እረገድም ጉልህ ድርሻ እንደነበራቸው ተገልጿል፡፡

እነዚህ የግል ጋዜጦች እራሳቸው ጥንፈኛ የፖለቲካ አቋም አራማጅ ሆነው የአገሪቱን የፖለቲካ አየር ከመበከል ይልቅ መንግሥትን በድፍረት የሚተቹትን ያህል ተቃዋሚውን ጐራ በተወሰነ ደረጃ በሃቅ የመገምገምና የመተቸት ድፍረት አግኝተው ቢሆን ኖሮ እስካሁን በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ የጐላ የተጠያቂነትና የግልፅነት ባህል እንዲዳብር በማድረግ በጐ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችሉ እንደነበር ግመገማው ጠቁሟል፡፡ እነዚህ የግል ጋዜጦች እንደ አንድ የፖለቲካ ተቋም የራሳቸውን ጥንፈኛ የፖለቲካ አመለካከት በሕዝቡ ላይ ለመጫን ከመሞከራቸውም በላይ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ይልቅ ሕዝቡን በራሳቸው አቅጣጫ የመምራት ሚና ይዘው የአገሪቱን ፖለቲካ ወደ አደገኛ አቅጣጫ እየገፉት እንደሆነና ይህም በዋናነት ከምርጫ 97 በኋላ ተቃዋሚዎች ፓርላማ እንዳይገቡና አዲስ አበባን እንዳይረከቡ በማድረግ ረገድ በግልፅ እንደታየ ተጠቁሟል፡፡ አብዛኛዎቹ የግል ጋዜጦች በዚህ ሁኔታ የሞያ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ባለመቻላቸውም ብዙውን ጊዜ መንግሥት በእነሱ ላይ ያልተቋረጠና ከመጠን ያለፈ አፈና እንዲፈፅምና የጠበቀ የፕሬስ ህግ እንዲያወጣም ምክንያት እንደሆኑት ግምገማው አሳይቷል፡፡ የጋዜጠኝነት ሥነ-ምግባርን አክብረው የሚሰሩ ጋዜጠኞች በአገራተን በብዛት ላለመኖራቸውም እስካሁን ጋዜጠኞችን በብቃት ለማሠልጠን የሚችል ጠንካራ ተቋም አገሪቱ ውስጥ አለመኖሩ አንድ ምክኒያት እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡

ስለሆነም በአንድ በኩል መንግሥት በሞኖፖል የያዘውን የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ተገቢ ከሆነ የቁጥጥር ሥርዓት ጋር ለውድድር ክፍት ካላደረገ፣ በአሁኑ ወቅት

በስራ ላይ የሚገኙ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃንም ከአንድ ፓርቲ ብቸኛ ቁጥጥር ወጥተው ሕዝቡን በገለልተኝነት ማገልገል የማይችሉ ከሆነ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የግል ጋዜጦችም የሞያውን ሥነ-ምግባር ጠብቀው ለሕዝቡ በገለልተኝነት ትክክለኛ መረጃ በማቀበል ኃላፊነታቸውን መወጣት የማይችሉ ከሆነ -በአገራችን ያሉ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃንም ሆኑ አብዛኛዎቹ የግል ጋዜጦች ሚናቸው ዴሞክራሲያዊ ሂደቱን ማገዝ ሳይሆን ማደናቀፍ ሆኖ እንደሚቀጥል ግምገማው ስጋቱን ገልፆ ተጠናቋል፡፡